የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራአራተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ ሚያዝያ ፫ ቀን ፪ሺ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No 21.
ADDIS ABABA 11th April, 2008

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፱/፪ሺ ዓ.ም

ለገጠር የኤሌክትሪክ አቅርቦት ማስፋፊያ ክፍል ሁለት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ...... ገጽ ፬ሺ፴፬

CONTENTS

Proclamation No. 569/2008

International Development Association Financing Agreement for Electricity Access (Rural) Expansion Phase II Project Ratification Proclamation Page 4034

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፱/፪ሺ

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለገጠር የኤሌክትሪክ አቅርቦት ማስፋፊያ ክፍል ሁለት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፹፮ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር /ሰማንያ ስድስት ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር/ የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ ጁላይ ፲፫ ቀን ፪ሺ፯ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፣

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፲፮ ቀን ፪ሺ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለገጠር የኤሌክትሪክ አቅርቦት ማስፋፊያ ክፍል ሁለት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፱/፪ሺ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 569/2008.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE FINANCING AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Financing Agreement between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit in an amount not exceeding SDR 86,000,000 (eighty six million Special Drawing Rights) for financing Electricity Access (Rural) Expansion Phase II Project was signed in Addis Ababa on the 13th day of July 2007;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the Financing Agreement at its session held on the 25th day of March, 2008;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub Article (1) and (12) of the Constitution it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Financing Agreement for Electricity Access (Rural) Expansion Phase II Project Ratification Proclamation No. 569/2008".

## ፪. የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ ጁላይ ፲፫ ቀን ፪ሺ፯ በአዲስ አበባ የተፈረመው ቁጥር 4344 ET የብድር ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን

የገንዘብና ኤኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፹፮ ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር /ሰማንያ ስድስት ሚሊዮን ኤስ.ዲ.አር./ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሚያዝያ ፫ ቀን ፪ሺህ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Ratification of the Agreement

The Financing Agreement Credit Number 4344 – ET signed in Addis Ababa on the 13th day of July 2007 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is hereby ratified.

## 3. Power of the Ministry of Finance and Economic Development

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Credit amount of 86,000,000 SDR (eighty six million Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Financing Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 11th day of April, 2008**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**